## <u>የውልቃይት ጠገዴ እሮሮ</u>

ከአሥረሥ አናጋው የተላከ (ከዳንሻ)

እናፅዳው ሥላችሁ፣ ግዴለም ስትሉ፣
ቢንቢ ሰፈረበት፣ ቀያችን በሙሉ።
ደርግስ ነግሮን ነበር፣ ከበራችን መጥቶ፣
ይኸው ቀለደብን፣ ወያኔ አዘናግቶ፣
የሚረጭ ጠፍቶ፣ ዲዲቲ ብናኝ፣
ሕዝቡን በቁም ፈታው፣ የወባ ትንኝ።

ተሐዲሶ ሥርዓት፣ ይበጃል እያሉ፣
የጋርዮሽ ሆነ፣ ከብቱም ሠውም ሁሉ።
እንዲህ ያለ ዘመን፣ የዘመን ቸነፈር፣
ለወያኔ ለማኝ፣ ሚስትንም መዘከር?!

አንድ ልጅ ተወልዶ፣ በዚህ በኛ መንደር፣
ማን ብለን እንጥራው፣ ተቸግሯል ሀገር?!

መንግሥት በኮሚቴ፣ እየተዳደረ፣
የፍክክር ደጃፍ፣ ሣይዘጋ አደረ።
"አልቅታም ወንዝና፣ ሹመ-ንዙ አገር፣
“ጥጃም አያሳድግ፣ ድሃም አያኖር፣"
ጥንት አባቶቻችን፣ ይነግሩን ነበር።
ጎበዝ ሞልቶ ተርፎ፣ ሳይጠፋ የሚያርሰው፣
እርሻችን ማሳችን፣ ዘመሚት ወረሰው፣
እንደት መለብለቢያ፣ ጭራሮ ያጣል ሰው።

ከእጃችን የወጣው፣ በእጅ እስኪመለስ፣
እናንተም ዝፈኑ፣ እኛም እናልቅስ።
አጋም የተጠጋው፣ ቁልቋል እስኪቆረጥ፣
ሲያለቅሱ መኖር ነው፣ ጤና ሳይለወጥ።